# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 244 ጥር 9 2005 ገጽ 1

ወያኔዎች ለወደፊቱ የአለም ቴክኖሎጂ ሲያድግ ህወሃቶች የተቀረውን የሀገራችንን ህዝብ አድልሆ በማድረግ አንድን ዘር በኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ የማሳደግ ስውር አጀንዳም ይዘው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ጥናቶች በተደጋጋሚ እያሳዩን ነው። ስለዚህ ይህንን የማስቆምና ዜጎች በሀገራቸው እንደዜጋ የሁሉም መብቶች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊውን መስዋእትነት በመክፈል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሁላችንም እንገባ ዘንድ የግድ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ዘረኝነት ፖሊሲ ትግርኛ የማይናገሩ ኢትዮጵያዉያንን የበይ ተመልካች እያደረገ መሆኑን የግንቦት 7 ጥናታዊ ሪፖረት አጋለጠ

ባለፈዉ ሳምንት ኢትዮ ተሌኮም ዉስጥ ስር እየሰደደ የመጣዉን የወያኔ ዘረኝነት በመረጃ በተደገፈ ጥናታዊ ዘገባ ለህዝብ ይፋ ያደረገዉ የግንቦት 7 የአገር ዉስጥ ኢንተሊጀንስ ዘርፍ በዛሬዉ ዕለት ደግሞ በተመሳሳይ ደረጃ አደረጃጀቱን፤ አወቃቀሩንና የሰዉ ኃይል አመዳደቡን ለአንድ አመት ሙሉ በቅርበት የተከታተለዉን የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺንን ጥናታዊ ዘገባ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ አድርጓል። ለኢትዮጵያ ከባድ እንዱስትሪ ግንባታ መሠረት ለመጣልና በአገሪቱ ኮንስትራክሺን እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ታስቦ የተዋቀረዉ የብረታብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺን የኢትዮጵያ መሆኑ ቀርቶ ሙሉ በሙሉ በትግርኛ ተናጋሪ የህወሀት መኮንኖች እጅ መግባቱን ያጋለጠዉ የኸዉ የግንቦት 7 ጥናት ኮርፖሬሺኑ ከዋና ዳይረክተር እስከ ተራ ቴክኒሺያኖች ስረስ የህወሀት አባል በሆኑ የትግራይ ተወላጆች ቁጥጥር ስር ወድቋል ብሏል። የጥናቱ ሙሉ ዘገባ እንደሚገተለው ቀርቧል።

## መነቀል ያለበት ስር የሰደደ የወያኔ ዘረኝነት

(በግንቦት 7 የአገር ዉስጥ ኢንተሊጀንስ ዘርፍ የተጠናና የተዘጋጀ)

ዘረኛዉ የወያኔ ስርአት የኢትዮጵያን ህዝብ ለጥቂት አመታት ኢትዮጵያዊያንን ባሰረና በገደለ ቁጥር ገንዘብ የሚሰጡትን አለም አቀፍ ድርጅቶችና አርዳታ ሰጪ አገሮች ደግሞ 21 አመት ሙሉ ካታለለበት መንገድ አንዱ የፌዴራል ስርአት መስርቼ ኢትዮጵያን የእኩሎች አገር አደረኳት የሚለዉ ባዶ አባባሉ ነዉ። ይህንን ተጋልጦ እርቃኑን የቀረ አባባል የኢትዮጵያ ህዝብ ተገንዝቦ ወያኔን መታገል ከጀመረ ቆይቷል፤ ዋና ዋናዎቹ እርዳታ ለጋሾችም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብ ደህንነት ግድ የሌለዉ ወያኔ ወጣቶቻችንን እየገበረ ጥቅማቸዉን ስለሚያስከብርላቸዉ ነዉ እንጂ ወያኔ እንኳን እየደገፉ እርዳታ የሚሰጡት በአንድ ተርታም አብረዉ ለመቀመጥ የማይመች የእኩዮች ስብስብ እንደሆነ ካወቁ ቆይቷል።

ህወሀት በፌዴራል ስርአቱ ዉስጥ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ምልክት ነዉ ብሎ በሚጠራዉ ፓርላማ ዉስጥ ያለዉ መቀመጫ 8 ብቻ ነዉ። እዚህ ፓርላማ ዉስጥ የትግራይን ህዝብ እወክላለሁ የሚለዉ ህወሀት ነዉ፤ ትግራይ ደግሞ ኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ክልል ናት። የተቀሩት 8 ክልሎች በዚህ የእኩልነት ምልክት በሆነዉ ፓርላማ ዉስጥ ያላቸዉ የመቀመጫ ብዛት 569 ነዉ። ሆኖም በወያኔ መንደር የፖለቲካ ስልጣን ምንጭ ህዝብ ሳይሆን ጠመንጃ ነዉና ወያኔ ፓርላማዉ ዉስጥ 8 ወንበር ብቻ ይዞ 569 ወንበር ያላቸዉን የኦሮሚያን፤ የአማራን፤ የደቡብ ክልልንና የተቀሩትን አምስት ክልሎች እንደ መኪና ይነዳቸዋል። የየክልሉን መሪ ይሾማል፤ ይሽራል ወይም የማይስማማዉን የክልል ባለስልጣን ያስራል። ፓርላማዉ ዉስጥ አንድ መቶ ሰባ ስምንት፤ አንድ መቶ ሰላሳ ስምንትና አንድ መቶ ሀያ ሦስት መቀመጫ ያላቸዉ የኦሮሚያ፤ የአማራና የደቡብ ክልል ፓርቲዎች በራሳቸዉ ጉልበትም ሆነ ህልዉና ስለሌላቸዉ አንዱ ከሌላዉ የበለጠ ስልጣን ወይም ሹመት ለማግኘት አንጋጥጠዉ ወደ ላይ የሚመለከቱት ህወሀትን ነዉ።

ለመሆኑ ወያኔ የፌዴራል ስርዐት መስርቼ የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት አረጋገጥኩ ሲል ምን ማለቱ ነዉ? እኩልነቱ የፖለቲካ ነዉ የኤኮኖሚ? ወይስ በየአመቱ ህዳር ወር ላይ የፌዴራልዝም ቀን ሲከበር እንደምናየዉ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት የተረጋገጠዉ በዘፈን ብቻ ነዉ? የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስርዐት ከላይና ከታች የሚቆጣጠረዉና ይህንኑ የፖለቲካ ስርአት የሚደግፍ የኤኮኖሚ መዋቅር ዘርግቶ የአገራችንን ኃብት የሚቦጠብጠዉ ህወሀት ብቻ ነዉና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ተረጋገጠ የሚባለዉ አባባል ከተራ የቃላት ድርደራ ዉጭ ሌላ ምንም ትርጉም የለዉም።

አፄ ቴዎድሮስን እንደ ልጅነት ሞዴሉ የሚመለከተዉ ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማሪያም የመጀመሪያዉን የኢትዮጳያ ዘመናዊ ወታደራዊ እንጂኔሪንግ ተቋም ሲመሰርት ስሙን "ጋፋት እንጂኔሪንግ" ብሎ ነበር የሰየመዉ። ስያሜዉ የአፄ ቴዎድሮስ ስራና ስም ህያዉ ሆኖ እንዲኖር ለማድረግ የተደረገ ሙከራ እንደነበር ግልጽ ነዉ። የኢትዮጵያን የቀድሞ መሪዎች በጅምላ የሚዘልፈዉ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ከአንዲት የአገር ዉስጥ ጋዜጠኛ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የእርቅ አባቶች እራሳቸዉ መታረቅ አቃታቸዉ- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ሲኖዶስ አሁንም ለሁለት እንደተከፈለ ነዉ

አገር ዉስጥና አገር ዉጭ በሚል ወያኔ ለሁለት የከፈለዉን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ሲኖዶስ አንድ ለማድረግ የተጀመረዉ ጥረት በወያኔ ጣልቃ ገብነት የተነሳ መክሸፉንና ከወያኔ አገዛዝ ጋር እጅና ጓንት የሆኑ አባቶች ተሰባስበዉ 6ኛዉን ፓትሪያሪክ መርጠዉ ለመሾም ዝግጅት መጀመራቸዉን አገር ቤት ላለዉ ሲኖደስ ቅርበት ያላቸዉ ምንጮቻችን ገለጹ። የዉጭዉ ሲኖዶስ ብጹዕ አቡነ መርቆሬዎስ አላግባብ የተቀሙት የፓትሪያሪክ ስልጣን ሊመለስላቸዉ ይገባል የሚል ጠንካራ አቋም ያለዉ ሲሆን አገር ዉስጥ ያለዉ ሲኖዶስ ግን አቡነ መርቆሬዎስ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በክብር እንዲኖሩ የቀረበዉን ሀሳብም አልቀበለም በማለቱ ሁለቱን ሲኖዶሶች ለማቀራረብ የተጀመረዉ ሽምግልና ያለ ዉጤት ተፈጽሟል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በውጪ ሃገር የሚገኘው ሲኖዶስ በአገር ውስጥ የሚደረግን የፓትርያርክ ምርጫ ያወገዘ ሲሆን እርቀ-ሰላሙ ያልተሳካውም ሆነ የፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ወደ መንበራቸው የመመለስ ጉዳይ ተቀባይነት ያላገኘው ቤተ-ክርስቲያንን ለማጥፋት ቆርጦ በተነሳው ኢህአዴግ የተባለ ሀይል ምክንያት ነው ሲል አስታውቋል።

በስደት ያለው ሲኖዶስ "ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ"በሚል ርዕስ ባወጣው ባለ 7 ገጽ መግለጫ ላይ፤ አራተኛው ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ በከፍተኛ ባለስልጣናትና ትዕዛዝ በወታደሮች ተገደው እንዴት ከቦታቸው እንዲነሱ እንደተደረጉ በስፋትና በጥልቀት አብራርቷል። ሀቁ ይህ በሆነበት ሁኔታ የአገር ቤቱ ሲኖዶስ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ አራተኛው ፓትርያርክ፡-"ስላመመኝ ስልጣኔን ተረከቡኝ ብለዋል>> ማለቱ ፈጽሞ ውሸት መሆኑን ያመለከተው በስደት ያለው ሲኖዶስ፤አንዲትም የድምጽ፣ የወረቀትም ሆነ የምስል ማስረጃ ማቅረብ በማይቻልበት ሁኔታ ህዝብን በሀሰት ማደናገሩ አግባብ እንዳልሆነ መክሯል። እርቀ ሰላሙ እንዲሳካ ላለፉት ሶስት ዓመታት በራሳቸው ተነሳሽነት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ለቆዩት የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች ጥልቅ ምስጋናውን ያቀረበው ሲኖዶሱ፤ አሁንም የቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ ከአገር ጉዳይ ተለይቶ የማይታይ በመሆኑ ሀገርን የምትወዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሲኖዶሱ ጎን እንድትቆሙ ጥሪ እናቀርባለን ብሏል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አዲስ አበባ ዉስጥ ያለዉ ሲኖዶስ የእርቅ ድርድሩ ያለዉጤት መጠናቀቁንና 6ኛዉን ፓትሪያሪክ ለመምረጥ በዝግጅት ላይ መሆኑን አስመልክቶ ያወጣዉ መግለጫ ኢትዮጳያን ጨምሮ በመላዉ አለም የሚገኙትን የተዋህዶ እምነት ተከታዮች እያነጋገረ መሆኑ ታወቋል። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑትና ወያኔ በግፍ 12 አመት በእስር ያንገላታቸዉ አባ አመሃ እየሱስ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ፣ በአዲስ አበባ ያለው እርቅ ያልተሳካው የሀይማኖት አባቶቹ የመንግስት ቅጥረኞች በመሆናቸው ነውም፣ ብለዋል።

## ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች አንድ ነን አንከፋፈልም አሉ

በትናንትናው እለት በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን "አንድነን አንከፋፈልም" በማለት የሰደቅና የአንድነት ፕሮግራም አዘጋጅተው መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ ። በትናንትናው እለት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በአዲስ አበባ በኑር መስጊድ በተካሄደው የሰደቃና  የአንድነት ስነስርአት ላይ መካፈላቸው የታወቀ ሲሆን ድርጊቱ ገዢው ፓርቲ ሙስሊሞችን ከሁለት ለመክፈል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለመቃም የታለመ መሆኑን በስነስርአቱ ላይ የተካፈሉ ሙስሊሞችን ያነጋገረው ዘጋቢያችን አመልክቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዘገባ፣ ተመሳሳይ ዝግጅቶች በሻሸመኔ፣ በጅማ እና በመቱ መካሄዳቸውን ጠቁሟል።

ይህ በንዲህ እያለ ኦሮሚያ የፕሬዚዳንት ያለህ እያለች መሆኑና - ፕረዚዳንት አለማየሁ አቶምሳ አሁንም ህክምና ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን በስልክ ያናገራቸው የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች ገለጹ። በ2002 ዓም የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሆኖ የተመረጠዉ አለማየሁ አቶምሳ ከተመረጠበት ማግስት ጀምሮ በህመም ምክንያት በስራዉ ላይ ለመገኘት ባለመቻሉና እሱን ለመተካት በኦህዴድ ባለስልጣናት መካከል ስምምነት በመጥፋቱ ኦሮሚያ ታይላንድ ሆስፒታል ዉስጥ ተኝቶ በሚታከም ፕሬዚዳንት መመራት ከጀመረች አመታት ያለፉ መሆኑን አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ አደራ ያሉ የኢህዴድ ከፍተኛ አመራር አባል በሰልክ የገለጹለት መሆኑን ዘጋቢያችን በላከው ሪፖርት አመልክቷል። የኦህዴድ ከፍተኛ አመራር አባለት ካለፈው ምክር ቤት ስብሰባ ጀምሮ አለማየሁ አቶምሳን ለመተካት በተደጋጋሚ ቢሰበሰቡም ከስምምነት ላይ መድረስ አለመቻላቸው ታውቋል። በመለስ ዜናዊ የቀብር ስነስርአት ላይ ለመገኘት ከሆስፒታል አልጋዉ ላይ ተነስቶ የመጣዉ አለማየሁ አቶምሳ የቀብር ስነስርአቱ ከተፈጸመ በኋላ ወድያዉኑ አቋርጦት የመጣውን ህክምና ለመከታተል ወደ ታይላንድ እንዳቀናና ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ግዜ ድረስ ታይላንድ ዉስጥ በህክምና ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

## እንደ መከላከያ ሁሉ ኢትዮ ቴሌኮምም

ዘረኛው የወያኔ መንግስት ዘረኝነቱን በሚያጠናክርለት ና የራሱን ጀሌዎች ብቻ የስርአቱ ተጠቃሚ በማድረግ የአንድ ብሄር የበላይነቱን ይዞ አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን የሚያሳይ ሌላ መረጃ ሰሙኑን የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ የጥናት ክፍል ይፋ አድርጓል ። ቀደም ሲልም በየካቲት 2002 በመከላከያ ሰራዊት በአዛዥነት ቦታዎች ያለውን የብሄር ተዋጽኦ ማጋለጣችን ይታወሳል።

ወያኔ በኢትዮ ቴሌኮም ውስጥ ለረጅም ግዜ በየዘርፉ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች አባሮና አፈናቅሎ ታማኝ ያላቸውን የህወሃት ታጋዮችን "ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ያስመረታቸውን ምርቶች እና ከመቀሌ ኢንስቲዩት ቴክኖሎጅ " በአብዛኛው ከአንድ ዘር በማምጣት መድቦ ኮርፖሬሽኑ የጀሮ መጥቢያ የስላላ ተቋምና የፓርቲው መሳሪያ በማድረግ የዜጎችን ሉዓላዊነት በመዳፈር ሀገራችንን በዚህ ዘመን የመረጃ ርሃብተኛ አድርጓታል።

በዚሁ ጥናት ሌላው አሳዛኙ ጉዳይ ከእያንዳንዱ 3.3 ሚሊዮን የኦሮሞ ተወላጅ ዉስጥ በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ የተሰጠዉ አንድ የኦሮሞ ተወላጅ ብቻ ሲሆን ትግራይን ስንመለከት ግን ከእያንዳንዱ 194 ሺ የትግራይ ተወላጅ ዉስጥ ቢያንስ አንድ ሰዉ በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ተቀምጧል። ይህ የስራ አመዳደብ የትምህርት ችሎታንና ልምድን ተከትሎ የተሰራ ነዉ ቢባል እንኳን የላቀ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ያላቸዉ የኦሮሞ ተወላጆች ቁጥር ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ካላቸዉ የትግራይ ተወላጆች ቁጥር በአስር እጥፍ መብለጡ ምንም ጥርጥር የለዉም።

ሌላው መራራ ሀቅ 66.2 በመቶ የሚሆነዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚያቅፉት ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል N1 በሚባለዉ ከፍተኛ የአመራር አርከን ዉስጥ በአመራር ቦታ የተቀመጡ ዜጎች ብዛት አራት ብቻ ነዉ (ሁለት ከኦሮሚያ ሁለት ከአማራ)። ከጠቅላላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዉስጥ 5.4 በመቶዉ ብቻ ከሚኖርበት ከትግራይ ክልል ግን ስምንት ሰዎች ኤን አንድ በሚባለዉ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ተቀምጠዋል።

ሌላው ወያኔዎች ለወደፊቱ የአለም ቴክኖሎጂ ሲያድግ ህወሃቶች የተቀረውን የሀገራችንን ህዝብ አድልሆ በማድረግ አንድን ዘር በኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ የማሳደግ ስውር አጀንዳም ይዘው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ጥናቶች በተደጋጋሚ እያሳዩን ነው። ስለዚህ ይህንን የማስቆምና ዜጎች በሀገራቸው እንደዜጋ የሁሉም መብቶች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊውን መስዋእትነት በመክፈል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሁላችንም እንገባ ዘንድ የግድ ነው።

ወያኔ/ህወሃት ለደረሰብኝ በደል ካሣ አሁን ተራዬን ሌሎችን የመበደል መብቴ ነው ብሎ የሚያደርገውን የአንድ ዘር የበላይነትንና ጨቋኝነቱን በድርጊቱ እንዲህ እየነገረን፤ በግልባጩ ግን ነጋ ጠባ የሚነገረን እኩል መሆናችንን ነው። ይህ ግን ሀሰት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጦልናል። በቀድሞ ሥርዓት የተበደለ በአዲሱ ሥርዓት በዳይ ሆኖ ቢገኝ ጥፋቱን አቅልሎ ማየት፤ የሥርዓት ለውጥ የበዳይና ተበዳይ ቦታ መለዋወጥ አድርጎ ከመገንዘብ የሚመጣ እጅግ አደገኛ የሆነ አመለካከት ነው እና የሀገራችን ህዝብ ይህንን አረመኔ ዘረኛ ስርአት ብሄራዊ አደጋ ውስጥ ሳያስገባን ልንታገለው ጊዜው አሁን ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ከእነዚህና ሌሎች እውነታዎች በመነሳት አሁን ግዜው የፍልሚያ ነው የሚለው፤ የቻለ በግንባር ያልቻለ በደጀንነት ይሰለፍ፣ ጠጠር ይወርውር ጠጠር ያቀብል! የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ሀገራችን ኢትዮጵያን ከሀገር በቀሉ ወራሪ ዘረኛ መንግስት የማዳን ጥሪ ጊዜው አሁን ነውና የምንችለውን ሁሉ በማድረግ የዜግነት ግዴታችንን እንወጣ! እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት የረጅሙ ጉዞ ምእራፍ አሁን ነው እና የአንድ ዘር የበላይ ዘረኝነት ፓሊሲን እንዋጋ!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

### ሰማያዊ ፓርቲ ኢህአዴግ በእስልምና እምነት ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት እንደሚቃወም ገለጠ

ሰማያዊ ፓርቲ ባወታው መግለጫ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ራሱ በህገ መንግስቱ የደነገጋችውን አንቀጾችና የእምነት ነጻነቶችን በመጣስ ባለፈው አንድ አመት በእስልምና እመነት ተከታዮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ችግር ፈጥሯል ብሎአል። አያይዞም የወያኔው ኢህአዴግ አገዛዝ የሙስሊሞች ተቃውሞ ከሽብር ጋር ይያያዛል በማለት ቢገልጽም እስካሁን በታየው እንቅስቃሴ ጉዳዩ ከሽብር ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የሚታይ ምንም ነገር የለም፣ ከዚያ ይልቅ በሚያስደንቅና ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ማቅረቡን ፓርቲው ለመገንዘብ መቻሉን ገልጿል።

ሰማያዊ ፓርቲ በመቀጠልም " ኢህአዴግ ጥያቄዎችን ያነሱት ጥቂት የስልጣን ጥም ያላቸው ግለሰቦች ናቸው ቢልም ባለፈው አንድ አመት ከተደረገው ሰላማዊ እንቅስቃሴ እጅግ ብዙ የእምነቱ ተከታዮች በወያኔ ኢህአዴግ ጣልቃ ገብነት ቅሬታቸው እንደገለጡ" ተረድቻለሁ ብሎአል።

የሙስሊም አመራሮችን በተመለከተም የታሰሩት የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት በራሱ በወያኔ እውቅና ተሰጥቷቸው ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ተደጋጋሚ ውይይት ማድረጋቸውን በማስታወስ፣ መሪዎቹ በተነሱት ነጥቦች ባለመግባባታቸው እና የደረሱበትን ለወከላቸው የእምነቱ ተከታዮች በማቅረባቸውና በአብዛኛው የእምነቱ ተካታዮች ዘንድ አመኔታ በማግኘታቸው ብቻ መታሰራቸው በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ቁጣ እያስከተለ መሆኑን ፓርቲው መገንዘቡን ገልጿል።

ሰማያዊ ፓርቲ "የኢህአዴግ መንግስት በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚያደርገው የሙብት አፈና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመምጣቱ ተቃውሞውም በዚያው ልክ እየጨመራና ቅርጽ እየያዘ መምጣቱን" በማስታወስ፣ ኢህአዴግ በሀይማኖት ጣልቃ መግባቱን እንዲያቆም፣ የታሰሩትም የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት እንዲፈቱ እንዲሁም ለጠፋው የሰው ህይወት ምክንያቱ እንዲጣራና ጥፋተኞች ለህግ እንዲቀርቡ ጠይቋል።

### ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ የወላይታ ተወላጆችን እያፈሰ ማሰር መጀመሩ ተሰማ

የኑሮ ፈተናቸዉን ለማሸነፍ አዲስ አበባ ዉስጥ በተለያዩ ጥቃቅን የንግድ ሰራዎች የተሰማሩ የወላይታ ተወላጆች "የጸጥታ ስጋት" ስለሆናችሁ ወደ መጣችሁበት አካባቢ መመለስ አለባችሁ በሚል በፌዴራል ፖሊስ እየታደኑ በመታሰር ላይ መሆነናቸዉን የአዲስ አበባ ዘጋቢያችን በያዝነዉ ሳምንት ላይ በላከልን ዘገባ ገለጸ።

የወላይታ ተወላጆች አዲስ አበባ ዉስጥ ከሚገኙት ሌሎች ብሔረሰቦች ተለይየዉ የጸጥታ ስጋት ሊሆኑ የቻሉበት ምክንያት ምን እንደሆነ ከወያኔ አገዛዝ የተሰጠ ማብራሪያ ባይኖርም በአሁኑ ወቅት ፖሊስ ከያሉበት እያፈሰ የሚያስረዉ የወላይታ ተወላጆችን ብቻ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፣ ፣ የአዲስ አበባዉ ዘጋቢያችን የፌዴራል ፖሊስ ምንጮችን ጠቅሶ በላከልን ዜና መሰረት ይህ ዜና እስከ ደረስን ጊዜ ድረስ 130 የወላይታ ተወላጆች ከአራት ኪሎ አካባቢ በፖሊስ ታፍሰዉ ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ ፖሊስ ጣቢያ ዉስጥ እንደታጎሩ ለማወቅተችሏል።

የፌዴራል ፖሊስ አፈሳዉን ባካሄደባቸዉ በአራት ኪሎና በሌሎቸም አካባቢዎች በርካታ በአነስተኛ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን አስሮ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የወሰደ ሲሆን ፖሊስ ጣቢያ ዉስጥ የታሳሪዎቹ መታወቂያ እየታየ የወላይታ ተወላጆች የሆኑት ታስረዉ እንዲቆዩ ሲደረግ የሌሎች ብሔረሰብ አባላት ግን ተለቅቀዉ ወደ ቤታቸዉ እንዲሄዱ መደረጉን አንድ በአፈሳዉና በምርመራዉ ላይ የተሳተፈ የፌዴራል ፖሊስ አባል በስልክ በሰጠን መረጃ ላይ ገልጿል።

የወላይታ አዉራጃ ከቆዳ ስፋቱ ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ የሚኖርበት አካባቢ በመሆኑ በየአመቱ በርካታ የአካባበዉ ተወላጆች ስራ ፍለጋ አዲስ አበባ፤ አዋሳና ሻሸመኔ በብዛት እንደሚመጡ ይታወቃል። የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ በሁለት እጥፍ አሳድግያለሁ የሚለዉ ወያኔ የህዝብን ችግር ከስሩና ከመንስኤዉ ከማሰወገድ ይልቅ ዉግያ የገጠመዉ ችግሩ ከፈጠረዉ ጠባሳ ጋር በመሆኑ የሚላስና የሚቀመስ አጥተዉ ሰራ ፍለጋ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚንከራተቱትን የወላይታ ተወላጆች ማሰር ጀምሯል። መለስ ዜናዊ በስልጣን ላይ በነበረባቸዉ ሃያ አንድ አመታት ዉስጥ ኢትዮጵያ ለትግርኛ ተናጋሪ የወያኔ ደጋፊዎች የምድር ላይ ገነት ሆና የቆየች ሲሆን ሀ/ማሪያም ደሳለኝ ስልጣን ከያዘ ገና አንድ አመት ሳይሞላዉ አሱ የመጣበት አዉራጃ ህዝብ እንደ አዉሬ እየታደነ ወደ ጫካህ ተመለስ ተብሎ በየፖሊስ ጣቢያዉ እንዲንከራተት መደረጉ ብዙዎችን ግራ ያጋባና ያነጋገረ ገጠመኝ ሆኗል።

ወያኔ አዲስ አበባን በተቆጣጠረባቸዉ የመጀሪያዎቹ ጥቂት አመታት ዉስጥ ተግባራዊ ካደረጋቸዉ አስቀያሚና ጎታች ፖሊሲዎች ዉሰጥ ዜጎችን "ወደ ተወለዳችሁበት አካባቢ" ሄዳችሁ ኑሩ የሚል ፖሊሲ ሲሆን ይህንን ፖሊሲ ተከትሎ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መታወቂያ ካርድ ላይ የዘር ማንነት እንዲቀመጥ አድርግዋል። ይህንን በሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተለይ የዘር ማጥፋት ወንጀል በተፈጸመባቸዉ እነ ሩዋንዳን በመሳሰሉ አገሮች ዉስጥ ታይቶ አጥፊነቱ የተመሰከረለትን ፖሊሲ ብዙ ኢትዮጵያዉያን በወቅቱ አምርረዉ መቃወማቸዉ ይታወሳል። ሆኖም ጠመንጃዉን የተማመነዉ ወያኔ ፖሊሲዉን ህዝብ ባይቀበለዉም በጉልበት ተግባራዊ አድርጓል። ወያኔ ይህንን የዘረኝነት ፖሊሲ ተግባራዊ ሲያደርግ አጅበዉ አይዞህ ያሉት እነ ሀ/ማሪያም ደሳለኝ "ቁጭ ብለው የሰቀሉትን ቆመዉ ማዉረድ አቃታቸዉ" እንደሚባለዉ ሆኖባቸዉ ጠ/ሚኒስትር የመሆን እድል ቢያገኙም ተወልደዉ ያደጉበት አካባቢህ ዝዝብ እንደ አዉሬ እየታደነ ወደጣህበት ጫካ ሂድ ሲባል ቁጭ ብለዉ እንደ ማንኛዉም ተመልካች ታዛቢ ከመሆን አላመለጡም።

---

## መነቀል ያለበት ስር የሰደደ የወያኔ ዘረኝነት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ጋር ባደረገዉ ቃለ ምልልስ አፄ ቴዎድሮስ ጋፋት ላይ ያሰሩትን መድፍና መንግስቱ ኃ/ማሪያም "ጋፋት እንጂኔሪንግ" ብሎ የሰየመዉን ወታራዊ ተቋም አስመልክቶ ሁለቱንም መሪዎች ሲያንቋሽሽ ተደምጧል። የሚገርመዉ ዛሬ ወያኔ የብረታብረት እንጂኔሪንግ ኮረፓሬሺን ብሎ የሚጠራዉ ግዙፍ የሲቪልና ወታደራዊ እንዱስትሪ ተቋምና በዚህ ተቋም ዉስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ፋብሪካዎች ደርግ "ጋፋት እንጂኔሪንግ" ብሎ የጀመራቸዉ የከባድ እንዱስትሪ ጅምሮች ናቸዉ። በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ "ጋፋት እንጂኔሪንግ" ስራዉን ሲጀምር የፋብሪካዉ ሀላፊዎች፤ እንጂኔሮች፤ የመምሪያ ሀላፊዎችና ቴክኒሺያኖች የስራ ዕድል የሚያኙት የትምህርት ደረጃቸዉ፤ ችሎታቸዉና የስራ ልምዳቸዉ ብቻ እየታየ ነበር፤ ወይም ትግርኛ ስለተናገረ ስራ የሚከለከል አማርኛ፤ ኦሮምኛ ወይም ሌላ ቋንቋ ስለተናገረ እድሎ የሚደረግለት ዜጋ አልነበረም። ዛሬ ወያኔ ከደርግ ስርአት ተረክቦ የብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን ብሎ በሰየመዉ እንዱስትሪ ዉስጥ አብዛኛዉን የሀላፊነት ቦታ የያዙ ሰዎች ለቦታዉ የበቁት በስራ ልምዳቸዉና ችሎታቸዉ ሳይሆን የተወለዱበት ዘርና የሚናገሩት ቋንቋ እየታየ ነዉ። ወታራዊዉ አምባገነን ደርግም ሆነ ወያኔ ይህንን እንዱስትሪ የወደፊቱ የኢትዮጵያ ከባድ እንዱስትሪ ዘርፍ መሰረት ይሆናል የሚል ራዕይ ነበራቸዉ። ልዩነታቸዉ የእንዱስትሪዉ አስፈላጊነት ላይ ሳይሆን እንዱስትሪዉን ማን ይቆጣጠረዋል የሚለዉ ጥያቄ ላይ ነዉ። ደርግ በሱ መሪነት ለማንም ችሎታ ላለዉ ኢትዮጵያዊ የእንዱስትሪዉን በር የከፈተ ሲሆን ወያኔ ግን እንዱስትሪዉ እንዳለ በአንድ ዘር ቁጥጥር ስር እንዲገባ አድርጓል። ደርግም ወያኔም አምባገነኖች ስለሆኑ አንዱስትሪዉን ከህዝብ ቁጥጥር ዉጭ አድርገዉታል፤ ወያኔ ግን ከአምባገነንም የጎሳ አምባገነን ስለሆነ ይህንን ትልቅ እንዱስትሪ ሙሉ በሙሉ በትግርኛ ተናጋሪዎች ቁጥጥር ስር አድርጎታል።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ባለፉት ሦስት አመታት ይህንን ወያኔ ገነባሁ የሚለዉን የፌዴራል ስርአትና በስርአቱ ዉስጥ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የሚጫወቱትን ሚና በመረጃ አስደግፎ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ አቅርቧል። የዛሬ ሁለት አመት ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያ መላከያ ሰራዊት ዉስጥ የተዘረጋዉን የወያኔ የዘረኝነት መረብ ከሰሞኑ ደግሞ የኢትዮቴሌኮምን የዘረኝነት አደረጃጀት በመረጃ በማስደገፍ ለህዝብ ማቅረቡ ይታወሳል። ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮረፓሬሺንን የዘረኝነት አደረጃጀትና በዚህ አደረጃጀት ዉስጥ ማን ምን እንደሆነ ያጣናዉን የጥናት ዉጤት በመረጃ አስደግፎ ያቀርባል። ግንቦት ሰባት ሃያ አራት ሰአት ሙሉ የሚከታተሉትን የወያኔ የደህንነት ሰራተኞች ከበባ ጥሶ የወያኔን ዘረኝነት የሚያጋልጡ መረጃዎችን ከራሱ ከወያኔ ጓዳ እየጎተተ አዉጥቶ ለህዝብ የሚያቀርበዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ዘረኝነት አያውቀዉም በሚል አስተሳሰብ አይደለም። ግንቦት ሰባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ የፈጠረዉ ከፍተኛ የመረጃ ጉድለት አለ ብሎ ያምናል፤ስለሆነም ህዝቡ የወያኔን ዘረኝነት ቢረዳም መጠኑን፤ ስፋቱንና ጥልቀቱን በሚገባ ላያዉቅ ይችላል ብለን እናምናለን። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በየቀኑ ደሙን እንደ መዥገር የሚመጠዉን ወያኔን የመሰለ የጀርባ ላይ አጥንት ተሸክሞ መኖር የለበትም ብለን ስለምናምን ህዝብን ለትግል ከምናዘጋጅበትና ከምናነሳሳባቸዉ መንዶች ዉስጥ አንዱ እንደዚህ ህዝብ በገዛ አገሩ "እኩል አደረግንህ" ብለዉ በሚነግሩት ከሀዲዎች ቅኝ አገዛዝ እየተገዛ መሆኑን በማሳወቅ ነዉ።

ባለፈዉ ሳምንት የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን ዋና ዳይረክተር ብርጋዴር ጄኔራል ክንፈ ዳኘዉ ፓርላማ ዉስጥ ተገኝቶ የኮርፓሬሺኑን የሁለት አመት የስራ ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት ኮርፓሬሺኑ የግል ባለኃብቶችን አያሳትፍም እንዳዉም እያቀጨጫቸዉ ነዉ፤ ለሙስና የተጋለጠ ነዉ፤ ደግሞም አብዛኛዉ የኮርፖሬሺኑ ሰራተኛ የመከላከያ ሰራዊት አባል ነዉና ይህ አሰራር ሠራተኞችን ለማስተዳደር አስቸጋሪ አይሆንም ወይ የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዉለት ነበር። የግሉን ዘርፍ መቅጨጭ በተመለከተ ኢትዮጵያ ዉስጥ ቀድሞዉንም ቢሆን "የወያኔ ዘርፍ" እንጂ የግል ዘርፍ የሚባል ነገር የለምና ጥያቄዉ መቅረብም አልነበረበትም። ሙስናም ቢሆን የወያኔ ስርዐት ዋናዉ መገለጫ ባህሪይ ስለሆነ ወያኔ እስካልተወገደ ድረስ ሙስና "ሙስናን እናጠፋለን" ስለተባለ ብቻ የሚጠፋ ነገር አይደለም። ግንቦት ሰባትን እጅግ በጣም ያሳዘነዉና ያስገረመዉ ነገር ያንን ወያኔ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ምልክት ነዉ ብሎ የሚናገርለትን ፓርላማ ያስጨነቀዉ (ተጨንቆ ከሆነ) የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺን በአንድ አናሳ ብሔረሰብ ሙሉ ቁጥጥር ስር መዉደቁ ሳይሆን አብዛኛዉ የኮርፖሬሺኑ ሰራተኞች የመከላከያ ሰራዊት አባላት መሆናቸዉ ነዉ። በእርግጥ የአንድ ትልቅ ኮርፖሬሺን ሰራተኞች በአብዛኛዉ የጦር ሠራዊት አባላት ሲሆኑ የአሰራርና የአስተዳደር ችግር መፈጠሩ አይቀርም፤ ሆኖም የሠራዊቱ ታማኝነት ለህዝብ ታዛዥነቱ ደግሞ ለህገ መንግሰስቱ ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህ ችግር በቀላሉ የሚወገድ ችግር ይሆን ነበር።
የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺን በአምሰት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሺን ፕላን ዉስጥ የሚጫወተዉን ቁልፍ ሚና ፓርላማዉ በሚገባ የሚገነዘበዉ ይመስለናል፤ ታዲያ ይህ በአገር እድገት ዉስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወተዉ ኮርፖሬሺን ሙሉ በሙሉ በአንድ ብሔር ቁጥጥር ስር ሲወድቅ ምነዉ የብሔረሰቦች እኩልነት ምልክት የሆነዉ ፓርላማ አፉን ዘግቶ ተመለከተ? ፓርላማዉን ይበልጥ የሚገድደዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በአንድ አናሳ ብሔረሰብ ሙሉ ቁጥጥር ስር ሆኖ ሌሎቹ ብሔረሰቦች ተመልካች ሲሆኑ ነዉ ወይስ የአንድ ኮርፖሬሺን ሰራተኞች በአብዛኛዉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ሲሆኑ ነዉ? ለመሆኑ የወያኔ ዘረኝነት በኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን ዉስጥ ምን ያህል ዘልቆ ገብቷል? የኦሮሞ፤ የአማራ፤ የሶማሌ፤ የሲዳማና ሌሎቹም ብሔር ብሔረሰቦች በዚህ ለአገር እድገት ቁልፍ በሆነ ኮርፖሬሺን ዉስጥ የሚጫወትቱት ሚና ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን በአስራ አንድ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን በስሩ አስራ ሦስት ግዙፍ እንዱስትሪዎቸን ያስተዳድራል፤ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ቁጥራቸዉ በዉል ተለይቶ ባይታወቅም አስራ ሦስቱ እንዱስትሪዎችም እያንዳንዳቸዉ በስራቸዉ ብዙ ፋብሪካዎችንና የማምረቻ ተቋሞችን ያቀፉ ናቸዉ። የኮርፖሬሺኑን አስራ አንድ ትላልቅ መምሪያዎችና አስራ ሦስት ግዙፍ እንዱሰትሪዎች በዋና ሀላፊነት፤ በዳይረክተርነተና በምክትል ዳይረክተርነት የሚመሩ 29 የከፍተኛ አመራር አባላት አሉ። ከእነዚህ 29 ከፍተኛ አመራር አባላት ዉስጥ 69 በመቶዉ ወይም ሃያዉ ህወሀት ሆን ብሎ ያስቀመጣቸዉ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ ወታደራዊ መኮንኖች ናቸዉ።በዚህ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች ያላቸዉ ቦታ 31 በመቶ ወይም ከእያንዳንዳቸዉ በቅደም ተከተል ሦስትና ስድስት ሰዎች ብቻ ሲሆን ከተቀሩት አምስት ክልሎች በዚህ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ የተመደበ አንድም ሰዉ የለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ እንዱስትሪ ለመገንባት በሚደረገዉ ጥረት ዉስጥ ከፍተኛዉን ሚና ይጫወታል የሚባለዉ የብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን በሲቪልና ወታራዊ መምሪያዎች ተከፋፍሎ የተዳራጀ ሲሆን በስሩ አስራ ሦስት ግዙፍ እንዱስትሪዎች ይገኛሉ። እነዚህን እንዱስትሪዎች በማስተዳደሩ በኩል የብሔር ብሔረሰቦችን ድርሻ ወይም ኮታ ስንመለከት ከአስራ ሦስቱ እንዱስትሪዎች ዘጠኙን የሚያስተዳድሩት የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። በኮርፖሬሺኑ ዉስጥ ከፍተኛ ስልጣን ከተሰጣቸዉ የትግራይ ተወላጆች ዉስጥ እነ ብረጋዴር ጄኔራል ክንፈ ዳኘዉ የብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺን ዋና ዳይረክተር ፤ ኮ/ል ተከስተ ኃ/ማሪያም በምክትል ዋና ዳይረክተር ማዕረግ የኮርፖሬት ፕሮዳክሺን ግንባታ ሀላፊ ፤ ኮ/ል ፀጋሉ ኪሮስ በምክትል ዋና ዳይረክተር ማዕረግ የኮርፖሬት ወታደራዊ ምርቶች ሀላፊ ፤ ኮ/ል ሙሉ ወ/ሰንበት በምክትል ዋና ዳይረክተር ማዕረግ የኮርፖሬት ፕሮጀክቶች አስተደዳደር ሀላፊ፤ሻምበል ካህሳይ ክሽን የምርመራና ልማት ዳይረክተርና ሻምበል ገ/ስላሴ ገ/ጊዮርጊስ የአቅም ግንባታና ስልጠና ማዕከል ዳይረክተርን የመሳሰሉ የህወሀት ታጋይ መኮንኖች ይገኙበታል።

ከትግራይ ዉጭ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔሰቦች በብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን እንዱስትሪዎች ዉስጥ ከፍተኛ የሀላፊነት ደረጃ ባለዉ የአመራር ቦታ ላይ የመቀመጥ ዕድል ያገኙ ኢትዮጵያዉያን ቁጥር አራት ብቻ ነዉ። ይህ ጥናት የተጠናዉ ከ2004 እስከ 2005 ዓም ባለዉ የአንድ አመት ግዜ ዉስጥ ነዉ። በ2004 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ 90 ሚሊዮን እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን ከዚህ ቁጥር ዉስጥ በትግራይ ክልል 5.4 ሚሊዮን ህዝብ በተቀሩት ስምንት ክልሎች ደጎሞ 84.6 ሚሊዮን ሀዝብ ይኖራል ተብሎ ተገምቷል። ይህ ጥናት በዋናነት የሚያመለክተዉ በዋና ዋና የሀላፊነት ቦታ የተቀመጡትን ግለሰቦችና ግለሰቦቹ የመጡበትን ብሔር ስለሆነ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺንን የሰዉ ኃይል ምደባና የደረጃ እድገትን ጠለቅ ብለን ስንመለከት አብዛኛዎቹ እንጂኔሮችና ቴክኒሻኖች የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ፤ የደረጃ እድገትን በተመለከተም ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ሲነፃፃር በፍጥነት የደረጃ እድገት የሚያገኙት እነዚሁ የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። ይህ ደግሞ በአጋጣሚ የሆነ ነገር ሳይሆን ወያኔ በረሀ ዉስጥ እያለ አቅዶት ባለፉት ሃያ አመታት በስራ ላይ ያዋለዉ የረጂም ግዜ እቅድና ዝግጅት ዉጤት ነዉ። ለምሳሌ ወያኔ ትግራይ ዉስጥ ኤም አይ ቲ ወይም የመቀሌ ቴክኖሎጂ እንስቲቲዩት ብሎ የሚጠራዉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋም ተቀብሎ የሚያስተምረዉ የትግራይ ተወላጆችን ሲሆን ከዚህ ተቋም የሚመረቁ እንጂኔሮችና ተክኒሺያኖች ናቸዉ በኢትዮጵያ ብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን የሚሊታሪ ክንፍና በኢትዮቴሌኮም የስለላ ተቋሞች ዉስጥ ተመድበዉ ከፍተኛ የስለላ ስራ የሚሰሩት።

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝና አገር ዉስጥና በዉጭ አገር የሚገኙ ቡችሎቹ የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይ በዳያስፖራ ዉስጥ የሚገኘዉን ለእናት አገሩ ተቆርቋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጅምላ "የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች" እያሉ ለአመታት ሲዘልፉን ኖረዋል። የፖለተካ ትግላችን አላማና ግብ ከጥላቻ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለዉ ቢሆንም - ለመሆኑ ይህንን በዘረኝነት ላይ የተመሰረተና አንዱን አለቃ ሌላዉን ተላላኪ፤ አንዱን የሚሾም ሌላዉን የሚሽር፤ አንዱን አብልቶ የሚያጠግብ ሌላዉን የበይ ተመልካች የሚያደርግ፤አንዱን የአገር መሪነት ቦታ ተረካቢ ሌላዉን ኮብልስቶን ድንጋይ ጠራቢ የሚያደርግ ስርዐት የሚወድ ማን አለ? ይህንን በንጹህ ዜጎች ደም እጁ የቆሸሰና ያደፈ ዘረኛ ስርአት ዉደዱ የሚለንስ ማነዉ? በምድርም በሰማይም የከሰሩ እነ ሚሚ ስብሀቱን (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## መነቀል ያለበት ስር የሰደደ የወያኔ ዘረኝነት . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

የመሳሰሉ የፖለቲካ ሴሰኞች ሊነግሩን እንደሚፈልጉት ትግላችን የትግራይ ወንድሞቻችንንና እቶቻችንን በመጥላት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የትግላችን ብቸኛ አላማ ከትግራይ ወንድሞቻችን ጋር ሊያጋጩን የሚሞክሩትን የህወሀት ወንጀለኞች አስወግደን ኢትዮጵያን የእኩሎች አገር ማድረግ ነዉ።

የብረታብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን መዋቅር ዉስጥ የዘርፍ ሀላፊዎች ዝርዝር

| ተ/ር | ስም | የሀላፊነት ቦታ | ብሔረሰብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ብረጋዴር ጄኔራል ከንፈ ዳኘው | የብረታ ብረት እንጂኔሪንግ ኮርፖሬሺን ዋና ዳይሬክተር | ትግሬ |
| 2 | ኮ/ል ሚካኤል ደስታ | ህዝብ ግንኙነት ዳይረክተር | አማራ |
| 3 | ኮ/ል መሐመድ | የህግ ጉዳዮች ጽ/ቤት ሀላፊ | ትግሬ |
| 4 | ሻምበል ደስታ | የጸጥታና ደህንነት ጽ/ቤት ሀላፊ | ትግሬ |
| 5 | ሻምበል ምናሉ ተሰማ | ጥራትና ቁጥጥር ኢንስቲትዩት ሀላፊ | ኦሮሞ |
| 6 | ሻምበል ካህሳይ ከሸን | ምርመራና ልማት ዳይረክተር | ትግሬ |
| 7 | ሻምበል ገ/ስላሴ ገ/ጊዮርጊስ | የአቅም ግንባታና ስልጠና ማዕከል | ትግሬ |
| 8 | ኮ/ል ሰሳይ ገ/መስቀል | የሴቶችና ህጻናት ቢሮ ዳይረክተር | ትግሬ |
| 9 | ኮ/ል ጽጌ አለማየሁ | የሰው ሀይል ዳይረክተር | ትግሬ |
| 10 | ኮ/ል ሸጋው ሙሉጌታ | የቦርድ ጽ/ቤት ሀላፊ | አማራ |
| 11 | ኮ/ል በርሄ | ምክትል ዋና ዳይረክተር-ፕሮጀክት ሎጂስቲክስ ሀላፊ | ትግሬ |
| 12 | ኮ/ል አብዱሰላም መሐመድ | ምክትል ዋና ዳይረክተር-ፕሮጀክት ፋይናንስና ኢንቨስትመንት ሀላፊ | አማራ |
| 13 | ኮ/ል ጠና ቁሩንዴ | ምክትል ዋና ዳይረክተር-የኮርፖሬት ሲቪል ምርቶች ሀላፊ | ኦሮሞ |
| 14 | ኮ/ል ተከስተ ኃ/ማሪያም | ምክትል ዋና ዳይረክተር-የኮርፖሬት ፕሮዳክሺን ግንባታ ሀላፊ | ትግሬ |
| 15 | ኮ/ል ፀጋሉ ኪሮስ | ምክትል ዋና ዳይረክተር-የኮርፖሬት ወታደራዊ ምርቶች ሀላፊ | ትግሬ |
| 16 | ኮ/ል ሙሉ ወ/ሰንበት | ምክትል ዋና ዳይረክተር-የኮርፖሬት ፕሮጀክቶች አስተዳደር ሀላፊ | ትግሬ |

በብረታብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን መዋቅር ዉስጥ የተለያዩ እንዱስትሪ ሀላፊዎች ዝርዝር

| ተ/ር | ስም | የሀላፊነት ቦታ | ብሔረሰብ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጋሻው እምሩ | ኢትዮ ፕላስቲክ እንዱስትሪ ሀላፊ | አማራ |
| 2 | መ/አ ሠለሞን ዘውዴ | ኬሚካልና ሲንቴቲክስ እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 3 | ኮ/ል ፍስሀ ግደይ | አዳማ ጋርመንት እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 4 | ኮ/ል ቢቱላ | የፋብሪኬ ንና ስትራክቸራል እንዱስትሪ ሀላፊ | ኦሮሞ |
| 5 | ሻለቃ መኮንን በላይ | ሜታልስ እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 6 | ኮ/ል ደሴ ዘለቀ | እርሻ መሳሪያዎች እንዱስትሪ ሀላፊ | አማራ |
| 7 | ሻምበል አሰፋ ዮሐንስ | ፓወር እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 8 | ኮ/ል ፀጋዬ አንሙት | ሀይቴክ እንዱስትሪ ሀላፊ | አማራ |
| 9 | ኮ/ል ሀድጉ በላይ | ሆሚቾ አሚዩኒሺን እንጂኔሪንግ እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 10 | ሻምበል ተሰማ ግደይ | ህብረት ማሺን ቱል እንጂኔሪንግ እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 11 | ኮ/ል ገ/መድህን ገ/ስላሤ | ቢሾፍቱ አቶሞቲቭና ሎኮሞቲቭ እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 12 | ሻለቃ ኢሉ ፀጋዬ | የደጀን አቪየሺን እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |
| 13 | ሻለቃ ግሩም ገ/መድህን | የጋፋት አርማመንብት እንዱስትሪ ሀላፊ | ትግራይ |

በብረታብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን መዋቅር ዉስጥ የተለያዩ እንዱስትሪ ሀላፊዎች ዝርዝር




የብረታብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፓሬሺን መዋቅር ዉስጥ የዘርፍ ሀላፊዎች ዝርዝር




### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org